በአካባቢው ነበሩ። ከእነርሱም መካከል ማርያም መግደላዊት፣ ማርያም የያዕቆብና የዮሴፍ እናት እንዲሁም የዘብዴዎስ ልጆች እናት ነበሩ።

ማቴዎስ 27:55-56

ጌታ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ወንዶቹ ፈርተው በተደበቁበት ጊዜ ሴቶቹ ደቀመዛሙርት ጌታን ሽቱ ለመቀባት ወደ መቃብሩ ሄዱ።

**ማቴ 27:61**

"መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛይቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ።"

---

ክርስቶስ ከሞት በተነሳ ጊዜ የመጀመሪያው የትንሣኤ ምሥክሮች ሴቶች ነበሩ። ወንዶቹ ደቀመዛሙርት ግን የሴቶቹን የአይን ምሥክርነት አንኳን አላመኑም።

ማር 16:1-9፤ ሉቃስ 24:1-12

እንዲሁም የጌታ ዳግም ምጽዓት በደጅ በሆነበት በዚህ ዘመን ሴቶች የጌታን ዳግም ምጽአት ለማፋጠን ትልቅ ሚና አላቸው። የጌታን ዳግም ምጽአት ማፋጠን የምንችለው፣ ራሳችንን ለታላቁ ተልዕኮ (ለሚሽን) በመስጠት ብቻ ነው።

"ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።"
(ማቴ 24:14)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከመወለዱ በፊት ጀምሮ፣ ሲወለድ፣ ከተወለደና አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ፣ ወደ ሞት ሲጓዝ፣ ሲሞት፣ ሲቀበር፣ ሞትን አሸንፎ ሲነሳ ሁሉ፤ ሴቶች ለጌታ ልብ ቅርብና ውድ የሆነ አገልግሎትን ሰጥተዋል። በዚህ ዘመንም ጌታ ከሴቶች ለልቡ የቀረበ ውድ አገልግሎትን ይጠብቃል።

የዚህ "ሴቶችን ለሚሽን" የሚል ጥሪ ዋና ዓላማ፤ ምንም እንኳን የኅብረተሰብ፣ የሃይማኖትና የባህል ተጽእኖ ቢኖርም፤ ሴቶች ከጌታ የተሰጣቸውን ጸጋና ጥሪ አንግበው ለታላቁ ተልዕኮ ሚሽን ራሳቸውን በመስጠት በክርስቶስ አካል ውስጥ የክብር በታቸውን በመያዝ እንዲበረታቱ ለመርዳት ነው።

"ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ
የሚማልዱኝ፥ የተበተኑት
ሴቶች ልጆቼ፥
ቍርባኔን ያመጡልኛል።"
ሶፎ 3:10

**"ብርሃንሽ መጥቶአልና፥የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፥ አብሪ።"**
ኢሳይያስ 60:1


**ሴቶችን ለሚሽን**

**+251-917-95127**

**info@globalgoodnews.org**
**www.globalgoodnews.org**
**Addis Ababa, Ethiopia**


# ሴቶችን ለሚሽን

- መላቀቅ ( ከአሉታዊ ተጽዕኖ)
- መያያዝ ( መንፈሳዊ ትስስር)
- መጸለይ (በግልም በኅብረትም)
- መገልገልና ማገልገል
- መስጠት/መሰጠት

**ግሎባል የምስራች ሚሽን የሴቶች አገልግሎት**

ሴቶች የመጸነስ፣ የመንከባከብ፣የማሳደግና የእግዚአብሔርን ዓላማና ሐሳብ ወደዚህ ዓለም የመውለድ ልዩ ጸጋና ችሎታ ከእግዚአብሔር ተቀብለዋል። የእግዚአብሔር ትልቁ ስጦታ የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ወደዚህ ዓለም የመጣው ከሴቲቱ ዘር ነው።
**(ዘፍ 3:15)**

የክርስቶስን የመጀመሪያ ምጽአት በምንመለከትበት ጊዜ፤ ሴቶች ክርስቶስ ከመወለዱ በፊትም ታላቅ ሚና እንደ ነበራቸው ከእግዚአብሔር ቃል እናነባለን።

በሉቃስ 2፥36-38 ነቢይቱ ሐና በወጣትነቷ ባልዋ ከሞተባት ጊዜ ጀምሮ 84 ዓመት እስከ ሚሆናት ድረስ በጾም በጸሎት በመቅደስ ሌትና ቀን ታገለግል እንደ ነበረ እናነባለን። ማርያምና ዮሴፍ ሕጻኑ ኢየሱስን ለጌታ የተቀደሰ ይሆን ዘንድ ወደ ቤተ - መቅደስ ሲወስዱትና ካህኑ ስምዖን በባረካቸው ጊዜ ሐና ፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር።
**(ሉቃ 2፥38)**

መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን መንገድ እንደ ጠረገ ሁሉ ነቢይቱ ሐናም ለስልሳ ዓመታት ያህል በጾም በጸሎት ሌትና ቀን በመቅደስ የኢየሩሳሌም ቤዛ የሆነውን የመሲሁን መንገድ ስትጠርግ ነበረ።

**“ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች፤ እርስዋም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች፤ እርስዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር። በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገ ር ነበር።”**
ሉቃስ 2፥36-38

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ባገለገለባቸው ጥቂት ዓመታት ውስጥ ጌታን በተለያየ መንገድ ከልባቸው ያገለገሉ ሴቶች በርካታ ነበሩ።

“ከዚህም በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር፤ አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥ የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐና ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።”

**ሉቃስ 8፥1-3**

የሰማሪያዊቷ ሴት፤ ጌታ የሰማሪያን ከተማ በሙሉ ለመድረስ የተጠቀመባት የከተማው ቁልፍ ነበረች፤ በሥጋ እናት ትሁን አትሁን ባናውቅም፤ በአንድ ጊዜ የከተማው ሁሉ መንፈሳዊ እናት ሆነች። ዋናው ቁም ነገር በሥጋ እናት መሆን ሳይሆን፣ መንፈሳዊ እናት መሆናችን ነው። ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ላሳያችሁ ብላ ገበናዋን ሳትደብቅ ጌታዋን በከተማው ሕዝብ ሁሉ ፊት አከበረች።

**“ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ለሰዎችም፣ ‘ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን’ አለች። ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።”
ዮሐ. 4፥28፡30**

በወንጌል ውስጥ የምናገኛት ሌላይቱ ሴት ደግሞ፤ የጌታ ኢየሱስን እግር በከበረ ሽቱ እየቀባች፣ በእንባዋ እያራሰች፣ በጸጉሯ እያበሰችና እየሳመች፣ እርሱ ራሱ እንደ መሰከረላት ከሞቱ በፊት ለመቃብሩ አዘጋጀችው።

“ከፈሪሳውያንም አንድ ከእርሱ ጋር ይበላ ዘንድ ለመነው፤ በፈሪሳዊው ቤትም ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ። እነሆም በዚያች ከተማ ኃጢአተኛ የነበረች አንዲት ሴት፤ በፈሪሳዊው ቤት በማዕድ እንደ ተቀመጠ ባወቀች ጊዜ፥ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ አመጣች። በስተ ኋላውም በእግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርስ ጀመረች፥ በራስ ጠጕርዋም ታብሰው እግሩንም ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበረች።” (ሉቃስ 7:36-38)

**በማቴዎስ ወንጌል እንዲህ በማለት ይመሠክርላታል**

“አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች በማዕድም ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተቈጡና። ይህ ጥፋት ለምንድር ነው፥ ይህ በብዙ ዋጋ ተሽጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና አሉ። ኢየሱስም ይህን አውቆ እንዲህ አላቸው። መልካም ሥራ ሠርታልኛለችና ሴቲቱን ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ፧ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም፤ እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።

**ማቴ 26:7-13**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ በሚሄድበት ጊዜ ብዙ ሴቶች ያገለግሉት ነበረ።

ከገሊላ የመጡና ኢየሱስን በሚያስፈልገው ነገር ለማገልገል የተከተሉት ብዙ ሴቶች ሁኔታውን ከርቀት እየተመለከቱ